# ሙዓለ፡ ንዋይ፡ ባንክ ምንድን፡ ነው ?

## What is an Investment Bank?

### የአክሰዮን ወይም የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች
Equity or Debt Securities




PRAGMA
INVESTMENT ADVISORY

<< swipe



ኢንቨስትመንት ስንል በተለምዶ “**ሙዓለ ንዋይን**” (ገንዘብን ስራ ላይ ማዋል) የሚልን ሃሳበ ለመግለጽ ስንፈልግ  የምንጠቀመው የእንግሊዝኛ ቃል ነው። ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጽንሰ ሃሳበ ጋር በተያያዘ ‹‹የኢንቨስትመንት ባንክ›› የሚለውን ስያሜ በቀጥታ ከመጠቀም ይልቅ ኢትዮጵያዊ ይዘት ያለው የአማርኛ ቃል ተጠቅመን ሰፊው የማህበረሰባችን ክፍል ሀሳቡን እንዲረዳው በማሰብ በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር  **፲፪፻፵፰/፳፻፲፫** ዓ.ም አንቀጽ **፴፬** ላይ ‹‹የኢንቨስትመንት ባንክ›› በሚል የተጠቀሰውን ሀረግ **ሙዓለ ንዋይ ባንክ** የሚል አቻ የአማርኛ ቃል ለመሰጠት ሞክረናል። በዚህ **መሰረት ሙዓለ ንዋይ ባንክ ማለት** ‹‹የኢንቨስትመንት ባንክ›› እንደሆነ ልብ ይበሉ።

Investment is a commonly used English word when we want to express the idea of “Investing money”. In order to use an Amharic word, we have tried to give an equivalent Amharic word for the phrase **Mual Nwai Bank** which is mentioned as “Investment Bank” in Article 34 of Ethiopian Capital Market Proclamation No.1248 /2021. Accordingly, **Mual Nwai Bank** is noted to mean “investment bank”.



**ሙዓለ ንዋይ ባንክ** ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውስጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢዎችን ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገዥዎች ጋር በማገናኘት የግብይት ስርዓቱ እንዲሳለጥ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ሚናን የሚጫዎት የገንዘብ ተቋም ነው። ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባንክ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ  አቅራቢዎች በኩል በመሆን የአቅራቢዎቹን ሰነዶች በማዘጋጀት እና በውክልና የመሸጥ አገልግሎት ይሰጣል በተጨማሪም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገዥዎች በኩል በመሆን ገዥዎችን በቀላሉ ከሰነድ ከአቅራቢዎች ጋር ያገናኛል።

An **investment bank** is a financial institution that connects securities issuers with buyers to facilitate the transaction in the capital market. Investment Bank acts as an advisor for security Issuer/ seller by  preparing and selling the securities on the issuer behalf to security buyers in the market,and plays a critical role as intermediary.



በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር  ፲፪፻፵፰/፳፻፲፫ ዓ.ም አንቀጽ ፴፬ መሰረት፤

**ሙዓለ ንዋይ ባንክ** ማለት ተቀማጭ ገንዘብ የማይሰበሰብ የገንዘብ ተቋም ሆኖ በሌሎች ድርጅቶች፣ በመንግሰት ወይም በሌላ ተቋም የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በውክልና በመሸጥ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪውን ከገዢ ሕብረተሰብ ጋር በማገናኘት ካፒታል በማሰባሰብ፣ የድርጅቶችን ውህደት እና ዳግም መልሶ የማዋቀር ሰራዎችን በማገዝ፣ ለደንበኞቹ እንደ አገናኝ  እና ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የአማካሪነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።

According to the  Ethiopian Capital Market Proclamation **No.1248 /2021** in article **34** the definition;

**Investment Bank** is a non-deposit taking financial institution that facilitates the creation of capital for other companies, governments, and other entities through underwriting, acting as an intermediary between a securities issuer and the investing public, facilitating mergers and other corporate reorganizations and acting as a broker or financial adviser for institutional clients.



# ዋና ዋና
# የሙዓለ ንዋይ ባንክ
# ስራና ተግባራቶች

## Major Investment Bank Operations and Activities.

PRAGMA
INVESTMENT ADVISORY



## የሙዓለ ንዋይ አማካሪ በመሆን ማገልገል።
## Serve as an Investment Advisor.

- ድርጅቶች የካፒታል ገበያ ላይ ብቁ ሆነው ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ቅድመ መስፈርቶች እንዲያሟሉ እና እንዲዘጋጁ ያማክራል።

  Advises companies to fulfill the regulatory requirement and prepare them to participate in the capital market.

- ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢዎቹ የተሰማሩበትን የንግድ ዘርፍ እና አዋጭነቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የሰነዶችን ዋጋ ይተምናል።

  Assessing the company’s performance, the business sector it operates in, and taking into consideration of current economic condition, investment bank will conduct valuation on the company’s securities.



# የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አገናኝ እና አከናዋኝ።
## ACT AS SECURITY BROKER AND DEALER.

- ሙዓለ ንዋይ ባንኮች በሰንደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውስጥ በድርጅቶች በኩል በሚሸጡ እና በሚገዙ  ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መካከል መካከለኛ (አገበያይ) ባንክ በመሆ ይሰራሉ።

  Investment banks are best known for their work as intermediaries between a security issuer and buyers in the capital market.

- እንዲሁም ለድርጅቶች ትልልቅ የሆኑ የብድር ሰነድ ገዥዎችን በማፈላለግ ለድርጅቶች ብድርን ያመቻቻሉ።

  They also arrange debt securities for corporations by finding large-scale investors for corporate bonds.



## በድርጅትም ሆነ በእምንግሰት ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በውክልን መሸጥ እና ማሳለጥ።

## FACILITATE AND UNDERWRITING SECURITIES FOR SALE BY COMPANIES AND GOVERNMENTS.

- ድርጅቶች ወይም በሌሎች ለመጀመሪያ እና ለሁለተኛ ዙር ለህዝብ ሽያጭ የሚቀርቡትን ሰነዶችን ለሽያጭ እንዲያወጡ ያደርጋሉ።

  They help companies or other security issuers (equity / debt) in the form of intial public offering (IPO) and secondery offering.

PRAGMA
INVESTMENT ADVISORY



## የሙዓለ ንዋይ እና የምጣኔ ሃብት ምርምር ማድረግ፡፡
## Conduct Investment and Economic Research

PRAGMA
INVESTMENT ADVISORY

Like & Share If You Found This Post Helpful.

PRAGMA
INVESTMENT ADVISORY
Your Vision, Our Process